የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለሥልጣን
ETHIOPIAN CAPITAL MARKET AUTHORITY

November 13,2026
Addis Ababa,Ethiopia

Ethiopian Capital Market Authority (ECMA) Grants License to Two New Investment Banks

The Ethiopian Capital Market Authority (ECMA) is pleased to announce the granting of investment banking license to **AMG Investment Bank PLC** and **NileBridge Investment Bank PLC** after a rigorous license application review process. In addition, the ECMA has approved the appointment of eight (8) Appointed Representatives and ten (10) board directors of the two newly licensed investment banks.

The Director General of the ECMA, Dagmawit Shiferaw, formally presented the license to the leadership of the two newly licensed investment banks during licensing event took place on Friday, 13 November 2026, at the ECMA's Head Office; increasing the total number of licensed CMSPs to twenty-three (23), and total number of Investment Banks to eleven (11).

During the licensing event, the Director General of the ECMA, Dagmawit Shiferaw, extended her congratulations to the newly licensed investment banks and urged the two licensees to fulfill their role in ensuring transparent and fair market transactions and promoting equitable distribution of wealth by providing market-standard professional services.

The ECMA extends its congratulations to **AMG Investment Bank** and **NileBridge Investment Bank** and reaffirms its commitment to a strong inclusive, and resilient capital market in Ethiopia.

For enquiries & additional information contact
Contact: Communications & Public Relations Directorate
Phone: 011 557 81 19
Email: communication@ecma.gov.et

የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለሥልጣን
ETHIOPIAN CAPITAL MARKET AUTHORITY

ህዳር 4፣ 2019 ዓ.ም
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለስልጣን ለ ሁለት አዲስ ኢንቨስትመንት ባንኮች ፈቃድ ሰጠ

የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለስልጣን ከሰፊ የፈቃድ ማመልከቻ ግምገማ ሂደት በኋላ **ለኤ ኤም ጂ ኢንቨስትመንት ባንክ ኃላ/የተ/የግ/ማ** እና ለ **ናይልብሪጅ ኢንቨስትመንት ባንክ ኃላ/የተ/የግ/ማ** የኢንቨስትመንት ባንክነት ፈቃድ መስጠቱን በደስታ ይገልጻል። በተጨማሪም ባለስልጣኑ የሁለቱን አዳዲስ ኢንቨስትመንት ባንኮች ስምንት (8) ተሿሚ እንደራሴዎች እና የአሥር (10) ቦርድ አባላት ሹመትን አጽድቋል።

የባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ጀነራል ዳግማዊት ሸፈራው ፈቃዱን ህዳር 4 ቀን 2019 ዓ.ም. በኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለስልጣን ዋና መስሪያ ቤት በተዘጋጀ መርሃ ግብር ለሁለቱ አዳዲስ የኢንቨስትመንት ባንክ አመራሮች በይፋ ያስረከቡ ሲሆን፤ በባለስልጣኑ ፈቃድ የተሰጣቸው የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጭዎች ጠቅላላ ቁጥር ወደ ሀያ ሦስት (23) ከፍ ሲል፤ የኢንቨስትመንት ባንኮች ቁጥር ወደ አስራ አንድ (11) ከፍ ብሏል።

በፈቃድ አሰጣጥ መርሃ ግብሩ ላይ የባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ጀነራል ዳግማዊት ሸፈራው በዕለቱ ፈቃድ ለተሰጣቸው የኢንቨስትመንት ባንኮች የእንኳን ደስ አላችሁ መልዕክት ያስተላለፉ ሲሆን፤ ኢንቨስትመንት ባንኮቹ ደረጃውን የጠበቀ ሙያዊ አገልግሎት በመስጠት በገበያው ላይ ግልጽ እና ፍትሀዊ ግብይት እንዲሰፍን እንዲሁም ፍትሀዊ የሀብት ክፍፍልን በማረጋገጥ ረገድ የበኩላቸውን ሚና እንዲወጡ አሳስበዋል።

የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለስልጣን በኢትዮጵያ ጠንካራ እና አካታች የካፒታል ገበያ ስርዓት እንዲገነባ ያለውን ቁርጠኝነት እየገለጸ **ኤ ኤም ጂ ኢንቨስትመንት ባንክን** እና **ናይልብሪጅ ኢንቨስትመንት ባንክን** እንኳን ደስ አላችሁ ለማለት ይወዳል።

ለጥያቄዎች እና ተጨማሪ መረጃ
የኮሙኒኬሽን እና የህዝብ ግንኙነት ዳይሬክቶሬት
ስልክ ቁጥር : 011 557 81 19
ኢሜይል: communication@ecma.gov.et